111324 እንግሊዝኛ

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

## ፍላሽ ካርዶች

adolescents and communities together

## የወይን ጠጅ ካርዶች

ሆርሞኖችን ሳይጠቀሙ እርግዝናን የመከላከል መንገዶች

## አረንጓዴ ካርዶች

ሆርሞኖችን በመጠቀም እርግዝናን የመከላከል መንገዶች

## ቀይ ካርዶች

በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች (STI) መከላከያ ዘዴዎች

አንዳንድ ዘዴዎች እርግዝናን መከላከል ይችላሉ

## ሰማያዊ ካርዶች

እርግዝናን በቋሚነት ለመከላከል የሚረዱ መንገዶች

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

## ዋናዋና መልዕክቶች

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

## ዋናዋና መልእክቶች

እያንዳንዱ ሰው የራሱ ሰውነትን በተመለከተ ውሳኔ የማድረግ መብት አለው። በታሪክ ውስጥ እና አንዳንድ ጊዜ አሁን ባለው የጤና አጠባበቅ መንገዶች፡ ጥቁር ቀለም ያላቸው ሰዎች፣ LGBTQ+ ሰዎች፣ እና ወጣቶች ሙሉ መብቶቻቸውን የማግኘት እድል የላቸውም። በትምህርት እና እርምጃ በመውሰድ ለውጥ እንዲመጣ ማድረግ እንችላለን። የስነ ተዋልዶ ፍትህን በተመለከተ የበለጠ ይወቁ፦ “Advocates for Youth” የተባለውን ድርጅት ይፈልጉ።

አንድ “የበለጠ ዘዴ” የለም - አንዳንድ ዘዴዎች የበለጠ ውጤታማ ናቸው - እንዲሁም እያንዳንዱ ሰው ለራሱ የሚበጀውን የመወሰን መብት አለው።

ዘዴው "99% ውጤታማ" ከሆነ ይህንን ዘዴ ለአንድ አመት ከሚጠቀሙት 100 ጥንዶች ውስጥ 99 ጥንዶች አያረግዙም ማለት ነው።

የጥበቃ ዘዴዎች  በአንዳንድ ሰዎች ላይ የጎንዮሽ ጉዳቶች ሊያስከትል ይችላል - ጥያቄዎች ካሉዎት የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ያነጋግሩ።

በእነዚህ ፍላሽ ካርዶች ላይ ያሉ ሁሉም ቋሚ ያልሆኑ ዘዴዎች በ Multnomah County Student Health Centers ውስጥ ያለምንም ክፍያ ይገኛሉ።

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

ከ STI መከላከል - እንዲሁም አንዳንድ ዘዴዎች እርግዝናን ሊከላከሉ ይችላሉ

# መታቀብ



- መታቀብ እርግዝናን ሊያስከትሉ ወይም በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመሰራጨት የሚችል ማንኛውንም የግብረ-ስጋ ግንኙነትን ማስወገድ ማለት ነው።
- መታቀብ፡ እርግዝናን ለመከላከል 100% ውጤታማ የሆነ ብቸኛው መንገድ ነው።
- መታቀብ ሰዎችን በግብረ ስጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች (STIs) ይከላከላል።
- ዕድሜ፣ ጾታ፣ የጾታ ዝንባሌ ወይም የጾታ ልምድ ሳይለይ፡ ማንኛውም ሰው መታቀብ ይችላል።

**100% ውጤታማ ነው**

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

## ሆርሞኖችን ሳይጠቀሙ እርግዝናን የመከላከል መንገዶች

# የማውጣት ዘዴ




- የማውጣት ዘዴው ከወንድ የሚወጣውን የዘር ፈሳሽ ከመፍሰሱ በፊት ብልቱ ከሴትዋ አካል ሲያስወጣ ነው።
- ያልተለመደ ቢሆንም፡ ወንዱ ከመጨረሱ በፊት ግንኙነቱ እርግዝናን ሊያስከትል ይችላል።
- ይህንን ዘዴ በትክክል ለመጠቀም ራስን ለመግታት መቻል እና በፍቅረኞች መካከል መተማመን ያስፈልጋል።
- የዘር ፈሳሽ መቼ እንደሚወጣ ለማወቅ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል።
- የማውጣት ዘዴው ከ STI በሽታ አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 78% ውጤታማ ነው**

# ከመዳብ የተሰራ INTRAUTERINE DEVICE (IUD)



- ከመዳብ የተሰራውን intrauterine device (IUD) ውስጥ ያለው ብረት የወንድ የዘር ፈሳሽ የመዋኛ መንገድን ይለውጣል፤ ስለዚህ ወደ እንቁላል መድረስ አይችልም። ሆርሞኖች የሉትም።
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢ IUD ን በማህጸን ውስጥ ያስገባዋል።
- አንዳንድ ሰዎች የአሰራር ሂደቱን የበለጠ ምቹ ለማድረግ መድሃኒት እንዲሰጣቸው ይጠይቃሉ።
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ከተፈጸመ በኋላ እርግዝናን ለመከላከል እስከ 5 ቀናት ድረስ ማስገባት ይቻላል እንዲሁም እስከ 12 ዓመታት ድረስ በቦታው ሊቆይ ይችላል።
- ሆርሞኖችን የማይጠቀም ብቸኛው የድንገተኛ የወሊድ መከላከያ ነው።
- ከመዳብ የተሰራውን IUD የአባላዘር በሽታዎችን አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፦ ከ 99% በላይ ውጤታማ ነው**

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

ሆርሞኖችን በመጠቀም እርግዝናን የመከላከል መንገዶች

# ሆርሞን ያለው INTRAUTERINE DEVICE (IUD)



- ይህ Intrauterine Device (IUD) የማህጸን አንገትን ፈሳሽ ለማወፈር ሆርሞኖችን ይጠቀማል፤ ይህም የወንድ የዘር ፍሬን ወደ እንቁላል እንዳይደርስ ይከላከላል። በ IUD ውስጥ ያሉ ሆርሞኖች እንቁላሎች ከማህጸን ውስጥ እንዳይወጡ ሊያስቆሙ ይችላሉ፤ ይህም ማለት አንድ የወንድ የዘር ፍሬ ለመፈልፈል የሚያስችለው ምንም እንቁላል አይኖርም።
- የጤና እንክብካቤ አቅራቢ IUDን በማህጸን ውስጥ ያስገባዋል፡ እና እንደ አይነቱ መሰረት፡ እስከ 8 አመታት ድረስ በቦታው ሊቆይ ይችላል።
- በወር አበባ ጊዜ የሰውነት ቁርጥማትን ሊያቃልል ይችላል፡ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የወር አበባን ሙሉ በሙሉ ያቆማል።
- ሆርሞን ያለው IUD የአባላዘር በሽታዎችን አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- ከ 99% በላይ ውጤታማ ነው**

# የወሊድ መከላከያ ክኒን




- እርግዝናን ለመከላከል የወሊድ መከላከያ ክኒን በየቀኑ በተመሳሳይ ጊዜ በአፍ ይወሰዳል።
- በመድሀኒቱ ውስጥ ያሉት ሆርሞኖች (ኢስትሮጅን እና/ወይም ፕሮጄስትሮን) የእንቁላል መውጣቱን ያቆማሉ፤ እንዲሁም እንቁላል እና ስፐርም እንዳይገናኙ ለማድረግ በማህጸኑ አንገት ላይ ያለውን ፈሳሽ እንዲበዛ ያደርጋሉ።
- ከ 50 በላይ “የክኒኑ” ብራንዶች አሉ።
- ለቁርጥማት፣ በብጉር፣ ለጡት እና ለማህጸን እብጠት እንዲሁም ለአይረን ማእድን እጥረት ሊረዳ ይችላል።
- የወሊድ መቆጣጠሪያ ክኒኑ የአባላዘር በሽታዎችን አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 91% ውጤታማ ነው**

# የወሊድ መከላከያ በመርፌ መወጋት



- የወሊድ መቆጣጠሪያ በመርፌ መወጋት እርግዝናን ለመከላከል ፕሮጄስቲን የተባለውን ሆርሞን ይጠቀማል፤ ይህም በማህጸን ጫፍ ያለውን ፈሳሽ በማወፈር እና ማህጸኑ እንቁላል እንዳይለቅ በማቆም ይከላከላል።
- እርግዝናን ለመከላከል የወሊድ መቆጣጠሪያው መርፌው በየ 3 ወሩ በክንድ ወይም በቂጥ ላይ መወጋት አለበት።
- የማህጸን ካንሰርን ይከላከላል እንዲሁም የወር አበባን ሙሉ በሙሉ ማቆም ይችላል።
- የወሊድ መቆጣጠሪያ መርፌው የአባላዘር በሽታዎችን አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 94% ውጤታማ ነው**

# የወሊድ መከላከያ መትከል



- የወሊድ መቆጣጠሪያ መትከል፡ በላይኛው ክንድ ላይ ከቆዳው ስር በሀኪም ወይም ነርስ የሚቀመጥ ትንሽ ተጣጣፊ የፕላስቲክ ዘንግ ነው። እርግዝናን ለመከላከል የሆርሞን ፕሮጄስትሮን ወደ ደም ውስጥ እንዲለቀቅ ያደርጋል።
- የወሊድ መቆጣጠሪያ መትከል እርግዝናን ይከላከላል፤ ይህም በማህጸኑ አንገት ላይ ያልውን ፈሳሽ በማወፈር እና ማህጸኑ እንቁላል እንዳይለቀቅ በማቆም ይከላከላል።
- ለ 5 ዓመታት ያህል በቦታው ሊቆይ ይችላል።
- ተከላው በወር አበባ ጊዜ የሰውነት ቁርጥማትን ሊያቃልል ይችላል፡ እንዲሁም አንዳንድ ጊዜ የወር አበባን ሙሉ በሙሉ ያቆማል።
- የወሊድ መቆጣጠሪያው መትከል የአባላዘር በሽታዎችን አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- ከ99% በላይ ውጤታማ ነው**

# የወሊድ መከላከያ ፕላስተር



- የወሊድ መቆጣጠሪያው ፕላስተር የሆርሞኖች ኢስትሮጅን እና ፕሮጄስትሮን በቆዳ (በእጅ ፣ በጀርባ፣ በቁጥ፣ ወይም በዳሌ) በኩል ወደ ሰውነት ይልካል።
- የማህጸን በር ጫፍ ያለው ፈሳሽ በማወፈር እና እንቁላል ከማህጸን ውስጥ እንዳይወጣ በማቆም፡ እንቁላል እና ስፐርም እንዳይገናኙ በማድረግ እርግዝናን ይከላከላል።
- ፕላስተሩ ለማግኘት የሀኪም ማዘዣ ያስፈልጋል፡ እንዲሁም በየሳምንቱ በተጠቃሚው መቀየር አለበት።
- ፕላስተሩ ለቁርጠት፣ ለብጉር፣ ለጡት እና ለማህጸን እብጠት፣ ለአይረን ማእድን እጥረት እና ለሌሎችም ሊረዳ ይችላል።
- የወሊድ መቆጣጠሪያው ፕላስተር ከ STI አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 91% ውጤታማ ነው**

# የኢሜርጀንሲ የወሊድ መከላከያ



- የኢሜርጀንሲ የወሊድ መከላከያ (EC) ከወንድ ብልት/የሴት ብልት የግብረ ስጋ ግንኙነት በኋላ እርግዝናን ለመከላከል የሚረዱ ዘዴዎችን ያመለክታል።
- ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ከተፈጸመ ከ 5 ቀናት በኋላ ከመዳብ የተሰራው IUD ማስገባት ይቻላል። ይህ በጣም ውጤታማው የ EC አይነት ነው።
- 2 ዓይነት የ EC ክኒኖች አሉ። ሁለቱም ክኒኖች እንቁላል እንዳይፈለፈል (የእንቁላል መለቀቅ) በመከላከል ወይም በማዘግየት ይሰራሉ።
- ከ 165 ፓውንድ በላይ ለሚመዝኑ ሰዎች ሆርሞን ያለበት EC ውጤታማነቱ ሊቀንስ ይችላል።
- EC ከ STI አይከላከልም።

**ወዲያውኑ ሲወሰድ የበለጠ ውጤታማ ይሆናል**

# የሴት ብልት ቀለበት



- የሴት ብልት ቀለበት በተጠቃሚው በሴት ብልት ውስጥ የሚቀመጥ ትንሽ ለስላሳ የፕላስቲክ ቀለበት ነው። በሴት ብልት ሽፋን ወደ ደም ውስጥ የሚገቡትን ኢስትሮጅን እና ፕሮጄስትሮን ሆርሞኖችን ያስወጣል።
- የማህጸን በር ጫፍ ያለው ፈሳሽ በማወፈር እና እንቁላል ከማህጸን ውስጥ እንዳይወጣ በማቆም፡ እንቁላል እና ስፐርም እንዳይገናኙ በማድረግ እርግዝናን ይከላከላል።
- ቀለበቱ ለማግኘት የሀኪም የመድሃኒት ማዘዣ ያስፈልጋል፡ እና በተጠቃሚው በየወሩ መቀየር አለበት።
- ቀለበቱ ለቁርጠት፣ ለብጉር፣ ለጡት እና ለማህጸን እብጠት፣ ለአይረን ማእድን  እጥረት፣ እና ሌላም ሊረዳ ይችላል።
- የሴት ብልት ቀለበት ከ STI አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 91% ውጤታማ ነው**

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

ከ STI መከላከል - እንዲሁም አንዳንድ ዘዴዎች እርግዝናን ሊከላከሉ ይችላሉ

# የላቴክስ እና የናይትሪል የእጅ መሸፈኛዎች



- የላቴክስ እና የናይትሪል የእጅ መሸፈኛዎች (የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች የሚጠቀሙት አይነት) ጣቶች እና እጆችን በሚጠቀሙበት ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት ከሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች (STIs) ጥበቃ ይሰጣሉ።
- አንዳንድ ሰዎች ላቴክስ ላይስማማቸው ይችላል - በምትኩ የናይትሪል ጓንቶችን ወይም የጣት ጫፍ ጓንቶችን ይጠቀሙ።
- በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ፡ በእነዚህ የእጅ መሸፈኛዎች ላይ፡ በውሃ ላይ የተመሰረቱ እና በሲሊኮን ላይ የተመሰረቱ ቅባቶች መጠቀም ይቻላል።
- ምርቱ የሚያበቃበትን ቀን እንዳላለፈ ማረጋገጥ አለቦት።
- እንደ ኮንዶም እና የደንታል መከላከያዎች የእጅ መሸፈኛዎች ለአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡ እና እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም።

# የደንታል ዳም (DENTAL DAM)



- ደንታል ዳም ቀጭን የላቴክስ ወይም ፖሊዩረቴን ያለ ወረቀት ሲሆን በአፍ በሚፈጸም የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎችን (STIs) መከላከል ይችላል።
- በአንድ ሰው አፍ እና በሌላው የሴት ብልት ወይም ፊንጢጣ መካከል እንደ መከላከያ ሆኖ ይቀመጣል።
- ደንታል ዳም እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የለባቸውም እንዲሁም ወደ ጎን ማዞር የለባቸውም።
- በማይክሮዌቭ የማይገቡ የፕላስቲክ መጠቅለያ እና የተቆረጠ ኮንዶም እንዲሁ እንደ ደንታል ዳም መጠቀም ይቻላል።

# የውስጥ ኮንዶም



- የውስጥ ኮንዶም አንዳንድ ጊዜ "የሴት" ኮንዶም ተብሎ የሚጠራው ከወሲብ በፊት ወደ ብልት ወይም ፊንጢጣ ውስጥ ለመግባት የተሰራ መከላከያ ነው። ከፖልይሪተይን (polyurethane) የተሰራ ውስጠኛ ቀለበት ያላቸው ከናይትሬል የተሰሩ ናቸው።
- የውስጥ ኮንዶም በፊንጢጣ እና በሴት ብልት ወሲብ ጊዜ መጠቀም ይቻላል። በሴት ብልት በሚደረገው ወሲብ ብቻ ኮንዶም ከግብረ ስጋ ግንኙነት በፊት እስከ 8 ሰአት ሊገባ ይችላል። የፊንጢጣ ወሲብ ጊዜ የውስጥ ቀለበት መውጣት አለበት። ኮንዶም እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።
- በኢንሹራንስ በኩል ወይም ከክሊኒክ በነጻ በኦንላይ ይገኛሉ።
- የውስጥ ኮንዶም ከእርግዝና እና ከ STI ይከላከላል።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 89% ውጤታማ ነው**

# የውጭ ኮንዶም



- የውጭ ኮንዶም አንዳንዴ "የወንድ" ኮንዶም ተብሎ የሚጠራው ቀጥ ያለ የወንድ ብልት ወይም የወሲብ መጫወቻ ላይ ለመገጣጠም የተነደፈ ቀጭን መሸፈኛ ነው።
- በአፍ፣ በሴት ብልት፣ ወይም በፊንጢጣ በሚደረጉ የወሲብ ግንኙነት ጊዜ መጠቀም ይቻላል።
- ከላቴክስ፣ ከፕላስቲክ፣ ወይም ከላምብስኪን ሊሰራ ይችላል።
- ኮንዶም እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የለበትም።
- ልምምድ ኮንዶም መጠቀምን ቀላል ያደርገዋል።
- በውሃ ላይ የተመሰረተ ወይም የሲሊኮን ቅባት የኮንዶም አጠቃቀምን የበለጠ ደህንነቱ የተጠበቀ እና የበለጠ አስደሳች ያደርገዋል።
- ከሙቀት እና ብርሃን በመራቅ (በኪስ ቦርሳ ውስጥ ሳይሆን) ያስቀምጡ።
- የላቴክስ እና የፕላስቲክ ኮንዶም ከእርግዝና እና ከ STI ይከላከላሉ።
- የላምብስኪን ኮንዶም ከ STI አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- 82% ውጤታማ ነው**

# የወሲብ ጤና ጥበቃ

እርግዝናን በቋሚነት ለመከላከል የሚረዱ መንገዶች

# TUBAL LIGATION




- Tubal ligation የወንድ የዘር ፍሬ ወደ እንቁላል እንዳይደርስ ተብሎ የማህጸን ቱቦዎችን ለመዝጋት በዶክተር የሚደረግ ለሁሉ ግዜ የማይቀየር ቀዶ ጥገና ነው። እንዲሁም "ቧንቧዎችን ማሰር" ተብሎም ይጠራል።
- ቀዶ ጥገናው ከተጠናቀቀ በኋላ እርግዝናን ለመከላከል እስከ 3 ወር ድረስ ሊወስድ ይችላል።
- Tubal ligations በግብረስጋ ግንኙነት የሚፈጠረውን ስሜት ወይም የወንድ ዘር ፈሳሽ ሲወጣ (እርካታ) ያለው ስሜት አይለውጡም።
- Tubal ligations ከ STI አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፦ ከ99% በላይ ውጤታማ ነው**

# ቫስክቶሚ




- ቫስክቶሚ የ vas deferens (የወንድ የዘር ፍሬን የሚወስዱ ቱቦዎች) በመቁረጥ እና በመዝጋት፡ ምንም ዓይነት የወንድ የዘር ፈሳሽ ወደ ዘር እንዳይጨመር የሚደረግ ቋሚ የሆነ ቀዶ ጥገና ነው።
- የአካባቢ ማደንዘዣ ይጠቀማሉ፡ ስለዚህ ሰዉ ነቅቶ እያለ ይደረጋል፡ ነገር ግን ህመም አይሰማውም። የቀዶ ጥገና ሂደቱ 15 ደቂቃ ያህል ይወስዳል።
- ቫስክቶሚ የተደረገላቸው ሰዎች አሁንም ኦርጋዝም አላቸው እናም የወንዱ የዘር ፈሳሽ ያወጣሉ፣ ነገር ግን ስፐርም የላቸውም።
- ከቀዶ ጥገናው በኋላ የዘር ፍሬው ከወንድ የዘር ፍሬ ነጻ ለመሆን 3 ወራት ያህል ይወስዳል።
- ቫስክቶሚ ከ STI አይከላከልም።

**የተለመደ አጠቃቀም፡- ከ99% በላይ ውጤታማ ነው**